# መቅድም

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ታሪክ ዘመንና መቼት ተሻግሮ የሚጣቀስ ሰፊ ደርዝ እና ረጅም ዕድሜ አለው። የተዋለደውም ወጥ ይዘት ባጀበው ቀጣይ ተግባር ሳይሆን ውስጣዊና ውጫዊ በሆኑ ዝብርቅርቅ ክንውኖችና ሂደቶች ተመጋጋቢነት ተለንቁጦ ነው። ዕናት፣ እልህና ተስፋ የሚቸሩ አኩሪ ክንውኖች፣ በተንጻሻም የተገቢና ተፈላጊ እርምት አስታዋሽ የሆኑ በደሎችና ውድቀቶች የተነባበሩበት ነው። እኛነታችንን በየዘመኑ ድርጊትና መስተጋብር በማየት ቀጣይነትንና ወቅታዊነትን ላጣጣመ ሚዛናዊ ግንዛቤ የሚያበቃ የጥንታዊና የዘመናዊ ሂደቶች ጥምረት ነው። ይሁንና በሚመጥን ክፍትነትና ህብራዊነት ተፈትሾ በአጎልባች መልኩ ከጥቅም ላይ እምብዛም አልዋለም። የተጠቀሰው የአጎልባች ፍተሻና ተጠቃሚነት እጥረትም በተለይ ከማንነት፣ ከአንድነትና ከሀገራዊ ህልውና ጋር በተያያዘ በስፋት የሚያጋጥም ነው።

በእነዚህ ዙሪያ የሚቀርቡ ትንታኔዎች በአመዛኙ "ታማኝነትና ከሃዲነት"፣ "አርበኝነትና ባንዳነት"፣ "ተቀጣሪነትና ፀረ ሀገርነት"፣ ወ.ዘ.ተ በሚሉ ፍፁም ተፃራሪ ብይኖች የተሞሉ ናቸው። የተሳታፊ ኃይሎች ሚና፣ ትብብሮችና ልዩነቶች እንዲሁም ለአሸናፊና ለተሸናፊነት ያበቃቸው ምክንያት ከየወቅቱ እውነታና ከምክንያታዊ ምዘና በራቀ መልኩ የሚቀርብበትም አጋጣሚ የበዛ ነው። ይህ ደግሞ ቀጥተኛ ተሳታፊ በመሆን የፖለቲካ ጥቅም ባገኙ ወይም እንዲያጡ በሆኑ ክፍሎች ዘንድ ብቻ ሳይሆን ለህብረተሰብና ለሀገር የተሟላ ታሪክን በትክክል የማቆየት ኃላፊነት የተሸከሙ ተመራማሪ ምሁራን ዘንድ ጭምር የተንሰራፋ ሆኖ እናገኘዋለን።

ይህም ከዘመናዊት ኢትዮጵያ የታሪክና የፖለቲካ ተዋስኦ ምክንያታዊነትን አስመንኖ መፈክራዊ ጠቅላይነትንና ስሜታዊ መካረርን ሊያነግስ በቅቷል። የተሟላ የታሪክ ጥናት ለማቅረብ ችሎታውም ሆነ ፍላጎቱ ያላነሳቸው ብዙዎችም በፍርሃት ዝምታንፕ አሊያም ጥናታቸው አከራካሪ ጭብጦችን ሳያነሳ ወይም ህያውን ዛሬ ሳይነካ እንዲቆም ያደረገ "ፈራ ተባ የሚል ድፍረት" ታሳሪ ሆነዋል። እንደ ህብረተሰብም ታሪካችንን በተሻለና በተሟላ ማወቅን እና ከዚህ የሚገኝ ብርታትን ተነፍገናል። የተቆመጠ ዕይታ ያመዘነበት ግንዛቤ ይዘን ለሙታን ተገቢ እረፍትና ክብር፣ ለህያዋን ደግሞ ተፈላጊ አቅም መንፈጊያ ግብዓት አድርገን ታሪካችንን አኮስስነዋል። በዚህ መልኩ የቀጠለው የኢትዮጵያ ሀገራዊ ታሪክ አጠቃቀምና ዕይታ መሞገትም መቀየርም አለበት። እውን እንዲሆን ግን ከጥቅል ትቅቅፍም ሆነ ውግዘት ነፃ በሆነ አጎልባች ምክንያታዊነት ሊፈተሽ ይገባዋል። ይህ መፅሐፍ ከዚህ እምነት የመነጨ ነው።

በታሪክ አቢሲኒያ በሚባለው ሰሜነኛ ማንነትና የተገደበ ግዛተ ክልል ይገለፅ የነበረው የጥንታዊት ኢትዮጵያ ሀገራዊነት በሁሉም ፈርጅ ስር ነቀል ለውጥ የተጎናፀፈው በአፄ ምኒልክ መስፋፋት ነበር። ለውጡ ሀገራዊነትን ለማደስ የሚያስችል አጋጣሚ እንዲሁም ፈተናን ያጣመረ ነበር። ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ቀጣይነት በጊዜው ተፈላጊ የሆነ አቅምና ነጻጅ

የቸረው ህብረ ብሔራዊ ጥንቅርና የሰፋ ግዛታዊ ቁመና የለውጡን አጎልባች ይዘት የሚገልፅ ነው። ከታሪክ አንፃር ዋነኛ መገለጫውም የወቅቱ ዓለም አንድ ኃያል በማንበርከክ የጥቁር ህዝቦች መኩሪያ ሊሆን የበቃው የአድዋ ድል ነው።

ህብረ ብሔራዊውን የኢትዮጵያ እውነታ የዳጠ የመገለልና አድልዖ ስርዓታዊ ሂደት ደግሞ በቀጣይ ዓመታት እየጨመረ የመጣ ፈታኝ ሀገራዊ ችግር ነበር። ይኸው ከኢትዮጵያ ህብራዊ ሁኔታ ተጣራሽ በሆነ ''አንድ ሀገር አንድ ህዝብ'' ርዕዮት ላይ የቆመ ወጥነት እና የጥቂቶች ጉልተኛ ተጠቃሚነት '**የማንበር**' ስርዓታዊ አካሄድም ለሀገራዊ ህልውና ነዳጅ የነበረውን የምኒልክ መስፋፋት ወደ ህልውና አናጊ ግብዓትነት ሊያሸጋግር በቃ። የዘመናዊት ኢትዮጵያ ሀገራዊ ግንባታ ሂደትም በተጨባጩ የኢትዮጵያ ህዝቦች ህብረ ብሔራዊ ማንነትና በሀገራዊ ውኁድነት መሀል '**ተመጋጋቢ ተደጋጋፊነትን**' መፍቀድም ሆነ መፍጠር አቅቶት በጋራ ትርጉምና ቁርኝት ላይ የቆመ ቀጣይ ሀገራዊ ህልውና የከበደው ሆነ።

በአፄ ኃይለሥላሴ ቀጥሎና ይበልጥ በደርግ ደንድኖ የኢትዮጵያን ሀገራዊነትና የህዝቦቿን ህልውና ከህልፈት አፋፍ ሊያደርስ በቃ። አንዱ ውጤትም፤ ከዚህ የተያያዘውን በደልና ተገላይነት ተቋቁሞ ህልውናን ለማዝለቅ በብሔር ማንነት ማዕቀፍ የተሰባሰበ ተቃውሞ ተፎካካሪ የፖለቲካ መስመር በመሆን ብቅ ማለት ነው። ከዚህ አኳያ ***ብሔር ተኮል የማንነት ፖለቲካ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ*** አንድ ***ውጤት*** ነው። ከ1983ዓ.ም ወዲህም የሀገራዊ ስርዓት ማዕቀፍ ሆኖ ይህንኑ ***የዘመናዊት ኢትዮጵያ*** ሀገራዊ የህልውና አደጋ በማለፍ ቀጣይነትን ለማረጋገጥ የዋለ አንድ ግብዓት ነው። በመሆኑም ***ብሔር ተኮል ማንነትና የኢትዮጵያ አንድነት ተፃራሪ የሆኑ ተጠፋፊዎች ሳይሆኑ*** በዚህ ተጨባጭ ማህበረ ፖለቲካዊ ሂደት የተሳሰሩ ***የኢትዮጵያ ሀገራዊ ታሪ***ክ ገፅታዎች ናቸው። በሌላ አባባል የብሔር ማንነትና ሀገራዊነት የኢትዮጵያ ውኁድ ህላዌ ተመጋጋቢ ተደጋጋፊዎች ናቸው።

በግንዛቤም ሆነ በአቋም ደረጃ የሚያጋጥሙ ***የኢትዮጵያ ሀገራዊነት ታሪክ ተፃራሪ ትርጓሜዎች*** ከዘመናዊት ኢትዮጵያ ግንባታ ሂደት የተመዘዙ መንታ ሰበዞች ናቸው። ይህ ግን በተመረጠ ዕይታ ወይም ጥቅል ፍረጃ ላይ በቆመ ትንታኔ በተገቢው ሊብራራ አይችልም። በተጨባጭ አስረጂዎች ለመደገፍ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ የተሳታፊ ተዋናዮችን ተመጋጋቢነት በትክክል ለመረዳት አያስችልም። ማህበረ ታሪካዊ ክንዋኔዎች የሌላቸውን *''ጥቁር''* ወይም *''ነጭ''* በሚል የተለየ ድንበር በማስቀመጥ የሚነሳ ዕይታ በመሆኑም የሂደቱን '**ግራጫ**' እውነታ የሚመጥን ክፍት ግንዛቤ ያራቀ ይሆናል።

የኤርትራ ጉዳይ በተለይ ይህንኑ ብሔራዊና ሀገራዊ ማንነት አጣጥሞ በመቀጠል እምቢተኝነት እና ከዚህ የመነጨ አዲስ መፍትሔ በማዋለድ መካከል የተካሄደ ግብግብ አመላካች ነው። በኃይል ሊታፈን የተሞከረ ፍላጎትና የይገባኛል ጥያቄ፣ ኃይል ጠቀስ እምቢታን በመውለድ የሚያጠናክርበት ተጨባጭ ሂደት አስረጂ ነው። የአንድ ዘመን

ውጤታማ ስልት የሁሌ እውነትና የትክክለኛ መፍትሔ ቁልፍ አለመሆኑ ፍንትው ብሎ የወጣበት ሂደት ነው። ስለራስም ሆነ ስለሌሎች ታሪክና ሁኔታ የተያዘ ግንዛቤ በየጊዜው በሀቅ ፈትሸው ካላረሙት ለዘላቂ ትርፍ የሚያበቃ እንዳልሆነ የሚያሳይ በቂ ትምህርት ባዘሉ ክንውኖች የተሞላ ነው። ህዝቦችና ሀገሮች በፖለቲካዊ ደረጃ መለየትና መዋሃድን መምረጣቸው የሚቻል ቢሆንም መልከዓ ምድራዊ በሆነ መልኩ የሚገለፀውን ጉርብትና በዘፈቀደ ሊያጠፉት እንደማይችሉም ጠቋሚ ነው።

በየጊዜው ለእርምት የሚያበቃ ተመጣጣኝና ተገቢ እርምጃ እስካልወሰዱ ድረስ ለሰላም የታቀደው ለግጭት፤ ለአሸናፊነት የታለመው ለሽንፈት ሊበቃ እንደሚችል አስታዋሽ ነው። በጭፍንና በትምክህት ለታጀበ የተናጠል የበላይነት የሚደረግ ጉዞ መጨረሻም አይቀሬ ውድቀት ሆኖ የመጠናቀቁ ዕድል ሰፊ መሆኑ በህያው ተሞክሮ አስረጂነት የቀረበበት ነው። አንድነት ከግዛታዊ ኩታ ገጠምነትና ከጥንታዊ የታሪክ ቁርኝት፤ ነፃነትም ከባንዲራ ማውለብለብ ባሻገርና በላይ ዘላቂነቱ ህያው ህዝቦችን የሚነካ ስራና እርምጃ እንደሚጠይቅ የሚያስተምር በደም የተፃፈ ድርሳን ነው።

ከዚህ አኳያ መፅሐፉ ከዘመናዊት ኢትዮጵያ ሀገራዊ ታሪክ ተያይዞ የሚነሳውን የኤርትራ ጉዳይ፣ የማንነት ፖለቲካ እና የልሂቁን ሚና በዋና አስረጂነት ያነሳል። ዘመን ተከል የሆኑ ርዕዮተዓለማዊ እምነቶች ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍ ሲል በጠቀስናቸው ጉዳዮች ዙሪያ የተወሰዱ እርምጃዎች እና የተያዙ አቋሞች መሰረታዊ መነሻ  አላቸው። ይህም ለታሪክና ማንነት ፍፁማዊ ወጥ ይዘትን የሚሰጥ፤ ዝግና የተቸከለ የአንድነት፣ የልዩነት፣ የፖለቲካ ግንኙነትና አሰላለፍ ወዘተ. ግንዛቤ ነው። ይህ ለታሪክና ማንነት ፍፁማዊ ወጥ ይዘት በመስጠት የሚነሳ ግንዛቤ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ ገዢ ስርዓታዊ መርህ ነበር።

በተወሰነ ደረጃ በ1966 አብዮት፤ በመሰረታዊ ደረጃ ደግሞ በ1983ዓ.ም በተካሄደው ሥርነቀል ስርዓታዊ መልሶ ማዋቀር ሥርዓታዊ መርህነቱ ተንዷል። ይሁንና ከአቀራረቡ ሶሻሊስታዊ ቋንቋ ባለፈ ሳይነካ በድህረ አብዮት ዓመታት ቀጥሏል። በድህረ ደርግ ዓመታትም መንግስታዊ ሥርዓቱን በሚመራው ክፍል ላይ ለሚሰነዘረው ተቃውሞ ገዢ አመለካከታዊ ማዕቀፍ በመሆን ሊንከባለል ችሏል። ለምንና እንዴት ይህ ሊሆን ቻለ? ሀገራዊ ታሪካችንን በተሟላ መልኩ ለመረዳት፤ ዋነኛ አደጋችንን ለይቶ በጋራ ግንዛቤና በተጨባጭ ስራ ቀጣይ ህልውናን ከማረጋገጥ አንፃርስ ውጤቱ ጠቃሚ ወይስ ጎጂና አደናቃፊ?

በሶስት ምዕራፎች በተካተቱ ስምንት ክፍሎች እነዚህንና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት ተደርጓል። ትንታኔያችን የዛሬውን እውነታ ተቀብሎ የሚነሳና የታሪክ ቅኝቱም መሰረታዊ የጋራ ጭብጦች ላይ ያተኮረ ነው። ትላንት ካደረግነው ወይም ካላደረግነው ተገቢውን ትምህርት የማግኘትና ለዛሬ ገንቢውን የማውጣት ፍተሻም ነው።

የሂደቱን ተሸጋጋሪ ፍሰት እንዲሁም አሉታዊና አዎንታዊ ገፅታ ለማየት የትንታኔው ንድፈ ኃሳባዊ መነሻ እና ማዕቀፍ በመፅሐፉ ክፍል አንድ ቀርቧል። የታሪክን ማህበረሰባዊ የሆነ የሰው ልጅ ውጤትነትና ንብረትነት በማንሳት በዚህ ውስጥ የሚስተዋለውን ትውልዳዊ ሚና ይተነትናል። ስለ ታሪካችን በአጠቃላይና ስለ ኤርትራ ጉዳይ በተለይ የሚንፀባረቁ የጋራ ጭብጦች በማስደገፍም ያለውን ግንዛቤያዊ ዋጋ ለማሳየት ተሞክሯል።

ክፍል ሁለት በታሪካዊ ጭብጦች ዋቢነት ከቅድመ ጣሊያን እስከ ፌዴሬሽን ፍፃሜ ባለው ሂደት ዋነኛ የሚባሉ ክንውኖችን ጠቅለል ባለ መልኩ ይዳስሳል። በየትኛውም የታሪክ ትንታኔ ላይ ተመስርተን ከሃዲና ታማኝ በሚል የምንፈርጃቸው የየትኛውም ጎራ መሪዎች ወይም የፖለቲካ ቡድኖች በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ተጋሪ የሆኑባቸው ክንውኖች እንዳሉ ለመጠቆም ይጥራል። ሂደቱም በሁሉም ደረጃ ወጥና ዝግ ፍረጃን የሚፃረር ተላላፊ ፍሰት የሚንፀባረቅበት እንደሆነ መሰረታዊ የሆኑ ወቅት ጠቀስ ክንውኖችና አካሄዶች በአስረጂነት አቅርቦ ያብራራል። አለፍ ሲልም በተፃራሪነት ቆምን የሚሉ ወገኖች ምን ያህል የአንድ ዓይነት አስተሳሰብ እና የመሰረታዊ እምነት ተጋሪዎች እንደሆኑ እና አንዱ ቆሜለታለሁ የሚለውን ግብ ይዞ ለተቃራኒው ወገን ግብ መሳካት አስተዋፅኦ እንዳደረገ እናይበታለን።

ይህን መሰረት በማድረግም በክፍል ሶስት እና በክፍል አራት፣ እንዴት አንድነት ብለን የኤርትራን ነፃነት እንዳፋጠንን የሚያሳዩ ጠቋሚ ጭብጦች ይነሳሉ። በተቃራኒውም ከእውነታው በተጣረሰ መልኩ *''ምንም ቁርኝት የሌለን ልዩዎች ነን''* በሚል አክራሪነት እንዴት የኤርትራ ፖለቲካ ኃይሎች ግብ ያሉትን ነፃነት እንዳዘገዩት እና እውን ከሆነም በኋላ፣ ምን ያህል ባንዲራን ከማውለብለብ ያለፈ ጣዕምና ዋጋ የሌለው ወደ መሆን እንዳወረዱት ይብራራል።

መሰረታዊ የሆኑ የተወሰኑ ግንዛቤዎች፣ ተሞክሮዎችና ግምቶች በምን መልኩ ለተሸጋጋሪነት በቅተው ከወቅታዊ እውነታዎች ጋር በመላቆጥ ለድህረ ነፃነት ሁኔታዎች መፈጠር ፍግ እንደሆኑም ለማየት ተሞክሯል። ከድህረ ነፃነት እስከ ባድመ ጦርነት ድረስ የታዩ ዋነኛ ክንውኖች በማስደገፍም የኢትዮጵያና ኤርትራ ግንኙነት መሰረታዊ ገፅታና ግንዛቤ ይፈተሻል። ይህም ከ1990 እስከ 1992ዓ.ም ከተካሄደው የኢትዮጵያና ኤርትራ ጦርነት እንዲሁም ከአልጀርስ እስከ ዛሬ ከታዩ ተግባሮች ጋር ተያይዞ የቀረበ ነው።

ያለፍንበት አፍራሽ ተሞክሮ ነገ እንዳይደገም እንዲሁም በቤተሰብ፣ በባህል፣ በቋንቋና በተወሰነ ታሪክ ተቋዳሽነት የደነደነውን የኢትዮጵያና ኤርትራ ጉርብትና እንዴት ለተሻለ ህይወት አቅም ማድረግ እንደሚቻል በክፍል አምስት ለማሳየት ተሞክሯል። በኢትዮጵያና ኤርትራ ልሂቃን ዘንድ በአጠቃላይ የሚታየውን ለውጥ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ መንግስት የቀረበውን የሰላም ሰነድ እንደ አንድ ግብዓት ወስዶ ያነሳል። ከኤርትራና ኢትዮጵያ ጉዳይ አንፃር የሚያጋጥሙ መሰረታዊ ትችቶችን በመንተራስም ያለውን ፋይዳ ይመዝናል።

ከዚህ በተያያዘም ከምንገኝበት ሀገራዊ፣ አካባቢያዊና ዓለማዊ ሁኔታ በተጣጣመ ጉዳዩን በዘላቂው ለመፍታት ያሉንን አማራጮች አጠር አድርጎ ይጠቁማል።

በዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ ልሂቁ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ይሁንና የዚህን ግዙፍ ሚና አሉታዊ ገፆች በመግለጥ የተማሪውን እንቅስቃሴ በቁርኝት የለሸ አውዳሚነትና ክህደት መፈረጅ የበዛ ነው። ይህ ፍረጃ በተለይ ከድህረ 1983ዓ.ም ወዲህ በአመዛኙ ተቀናቃኝ ልሂቅ እና ደጋፊዎች ዘንድ የይዘት ተመሳሳይነቱ በጎላ መጠን እየጨመረ የመጣ ነው። ማዕከላዊ ነጥቡም ከተማሪው እንቅስቃሴ የወጣው ልሂቅ ማርክሲስታዊ ርዕዮት መተቃቀፍ *"የብሔር ፖለቲካን ለመንተት እና ኢትዮጵያን ለመበታተን"* ምክንያት ሆኗል የሚል ነው። ያዘለው እንደምታም የብሔር ጥያቄም ሆነ መገንጠል ከኢትዮጵያ ታሪክ ሂደት ያልተያያዘ እና በጥቂቶች የተፈበረከ የሚል ድምዳሜ ነው።

የልሂቁ ግራ ዘመም ፖለቲካ ከዘመኑ ብቻ ሳይሆን፣ በዋናነት በሁሉም ደረጃ በአናጊ ክፍተት ከሚገለፀው የወቅቱ የኢትዮጵያ ማህበረ ህሊናዊ ሁኔታ እና ከተጋፈጠው ተጨባጭ ችግሮች የመነጨ ተገቢ ተመራጭነት የነበረው ነው። የኢትዮጵያ ሀገራዊ ህልውና ሊቀጥል ተችሎት ለዛሬ የበቃው በተማሪው እንቅስቃሴ ልሂቅ እና የማርክሲስት ርዕዮት ታሪካዊ መገጣጠም የቀረፀው ፖለቲካዊ ስብዕና ከጠባብ ብሔረተኝነት ለዘለለ ዕይታና ትብብር የተመቸ በመሆኑ ነው (የታየበት የግትርነት፣ መፈክራዊ አነባናቢነት፣ ጥቅል የሆነ የትላንት ድምሰሳው ወዘተ... እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው)። መፅሐፉ በምዕራፍ ሁለት፣ ክፍል ስድስት እና ሰባት ይህንኑ ነጥብ በታሪክ አስረጂዎች አስደግፎ ይተነትናል። ይህም ከሀገራዊ ለውጥ በተያያዘ ከአልጋ ወራሽ ተፈሪ እስከ ዛሬ የኢትዮጵያን ልሂቅ ባለፈበት ሂደት የሚገኙ መሰረታዊ ክንውኖች በመቃኘት የቀረበ ነው።

በማንነት፣ በአንድነት፣ በልዩነትና ትብብር ወዘተ. ጉዳዮች ዙሪያ የተስተዋለው የተቸከለ ፖለቲካ መንስኤ የሆነው ኢምክንያታዊ ጠቅላይ አስተሳሰብ መሰረታዊ መነሻ አለው። ታሪክንና ማህበራዊ መስተጋብርን ፍፁማዊና ዝግ በማድረግ የሚነሳ የተቆመጠ ግንዛቤ ነው። ለስኬት የበቁ ውሱን ሂደቶች በፍግነት ተጠቅሞ እና የመለየት አስፈሪነት ያበራታውን የመመሳሰል ቅብብሎሽ ተንተርሶ ለመቀጠልም ችሏል። በምዕራፍ ሶስት ክፍል ስምንት፣ የዚህ ግንዛቤ መሰረታዊ አንጓዎች በትላንት እና በዛሬ አስረጂ ጭብጦች ደጋፊነት ይተነተናሉ። ከተነሱት ታሪካዊ ጭብጦች የተያያዙ የጋራ ነጥቦችም ለማስቀመጥ ተሞክሯል። ከዘመናዊት ኢትዮጵያ ተጨባጭ የታሪክ ሂደት እንዲሁም ከዴሞክራሲ ፖለቲካ እና የኢኮኖሚ እድገት ጋር ያላቸው ተጣጣሚነት ይሞገታል። ያላቸው እንደምታም ተዳስሷል።

የኢትዮጵያ በዛ ያልን ልሂቃን በለመድነው ፍፁማዊ ዝግ የታሪክና የማንነት ዕይታ መቀጠል፤ ለእውነትም ሆነ ለፍሬያማነት የሚያቀርብ አይደለም። ለታሪክ ታማኝነትም ሆነ ለተሻለ ህይወት አያበቃም። ይልቁንም የጥንታዊ ሥልጣኔ፣ የኩሩ ታሪክ እና የብዙ አዋቂዎች ባለቤት ነን ለምንል ህዝቦች የማይመጥን የውድቀት ጉዞ ከመሆን አያልፍም።

ከኢትዮጵያ ሀገራዊ ታሪክ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በየወቅቱ በመፈተሽ ህልውናችንን በዘላቂ መሰረት ላይ ማቆም ይገባናል።

ዋነኛ ችግሮቻችን በሆኑት የልማትና የዴሞክራሲ ስራዎች ላይ በተናጠልና በጋራ እንድናተኩር፣ መጪው ትውልድም ''ከተሸጋጋሪ እዳዎች'' ነፃ እንዲሆን የሚያስችል አዲስ ምዕራፍ መክፈትና ቀጣይ መሰረት መጣል ይኖርብናል። የአንድ ትውልድ ልሂቅ መሆን በሁሉም ሀገራዊ ጉዳዮቻችን ዙሪያ ይህን መሰል ሽንቋጭ ጥያቄዎችን በድፍረት ማንሳት፤ አንስቶም ግልፅ ምላሽ በመስጠት የነገ አመላካች መሪነት ሚና መወጣትን ግድ ይላል። በየዘመኑ በተንከባላይ ችግሮች የተነሳ ትውልዶች መገበርን አቁመው፤ ዛሬ የእድገት፣ የዴሞክራሲና የሰላም ፍሬ የሚያጣጥሙ ሀገሮች ለዚህ የበቁት ልሂቆቻቸው ግንባር ቀደም አጋፋሪ ስለሆኑላቸው ነው። ሌላ ምንም የተሰወረ ምስጢር የለውም።

ይህ መፅሐፍ ''በአካዳሚያዊ ምርምር ዘርፍ የተለመደውን የምሁራዊ ጥናት መስፈርት'' ባሟላ መልኩ የቀረበ አይደለም። ከዚህ የሚመነጭ ''አዲስ ግኝት'' ይዞ ብቅ ያለም አይደለም። ከፍ ካለ ይህን ''አማትሮ የመቀላወጥ''፣ ዝቅ ሲል ደግሞ በጉዳዩ ዙሪያ የፀሐፊውን የታሪካችን ዕይታ ይዞ በመቅረብ አቅሙ ያላቸውን የመኮርኮር ጩኸት ነው። ለፍተሻና ለለውጥ የሚያበቃ አጎልባች ክርክር መጫርም ግቡ ነው። የዛኑም ያህል ከመረጃና ከምክንያታዊነት ተጣጣሚ የሆኑ ትርጉሞችን ደግፎ የቆመ መሆኑን አንባቢው ማየት ይችላል። በሁሉም ደረጃ ግን ከታሪካችን የተሟላ ንባብ መንጭቶ የተደረሰበት ድምዳሜ ሆኖ ወገናዊ ጎርባጭነት እንዳይኖረው፤ መጎርበጡ አይቀሬ ከሆነ ደግሞ ልንታረቀው የሚገባ የታሪካችንና ማንነታችን ሀቅ ነው በሚል እምነት የቀረበ ነው።

በምንጭነት ከጥቅም ላይ የዋሉ ስራዎች በአጠቃላይ የፀሐፊዎቻቸውን ገኃድም ሆነ እምቅ መልእክት ይዘት እንደጠበቁ ለመውሰድ በተቻለ መጠን ተሞክሯል። ከጥቅሶች ከተያያዙ ቀናት በስተቀር በመፅሐፉ የተጠቀሱ ዓመተ ምህረቶች በሙሉ የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የተከተሉ ናቸው። ከዚህ በመለስ በፅሑፉ ለሚያጋጥሙ ግድፈቶች፤ እምነት ነክ ትርጓሜዎችና ገለፃዎች ኃላፊነቱ ሙሉ በሙሉ የፀሐፊው ብቻ ነው። ፅሑፉን በትእግስትና በውል እንዲያነቡት አደራ እላለሁ። መልካም ንባብ...